## ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ እና የኢትዮጵያ ብራና መጻህፍት ማይክሮፊልም ድርጅት

ዶ/ር ሥርግው በዩኒቨርሲቲ መምህርነትና በታሪክ ደራሲነት ካበረከትዋቸው ጠቃሚ ክቡር ስራዎች ሌላ የተጠቀሰው ድርጅት እንዲመሰረትና እንዲቁዋቁዋም የሀሳቡ አመንጪ በመሆን ባደረጉት ጥረት፣ ሀሳባቸው በመንግሥት እና በቤተ ክህነት ተጠንቶና ተደጋፊነትን አግኝቶ ሊቁዋቁዋም ችልዋል። ከድርጅቱም ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ዶ/ር ሥርግው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ስራዎች ከ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ጀምሮ አከናውነዋል።

1. የድርጅቱ የመጀመሪያ ስራአስኪያጅ በመሆን፡ ለሥራው የሚይመቹ ቢሮዎች፣ ቁዋሚና አላቂ መሳሪይዎች እንዲሙዋሉ አድርገዋል።
2. የውጭ አገር የገንዘብ ርዳታ በማጠያየቅ ከፎርድ ፋውንዴሽን ለዋናው ስራ ማስጀመሪያ የገንዘብ ርዳታ አስገኝተዋል።
3. ሠራተኞችን በቴክኒክ የሚያሰለጥኑና የማይክሮፊልም ሥራውን የሚያስተምሩ የውጭ ኤክስፐርቶች ተቀጥረው እንዲመጡ አድርገዋል።
4. ለድርጅቱ ባስገዙት ላንድሮቨር መኪና በየክፍላተ ሀገሩ ከሚገኙት ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ጥንታውያን የብራና መጻህፍት ወደ ማእከሉ በብዛት እየመጡ በምይክሮፊልም እየቀረጹ እንዲመለሱ በማድረግ ስራውን በጥንቃቄ እንዲከናወን መርተዋል።
5. በየገዳማቱ በአቀማመጥ የተጎዱት ብራና መጻህፍት በጥንቃቄ እንዲጠገኑ ጥራዛቸውም እንዲታደስና እንዲስተካከል አድርሰዋል።
6. እስከ ፲፱፻፸ ዓ. ም. ድረስ ድርጅቱ በዶ/ር ሥርግው አመራር ባስገኘው አመርቂ ውጤት እስከ ስምንት ሺህ የሚደርሱ የብራና መጻህፍት በማይክሮፊልም ተቀርጸው ቅጃቸው በተስማሚ ቦታ ሊቀመጥ ችለዋል።
7. የእያንዳንዱ መጽሀፍ ይዘት፡ በላዩ ያለው ተጨማሪ ማስታወሻ፡ እድሜ፣ ወዘተ... ተገልጾ የተዘረዘረበት ካታሎግ ከተዘጋጀ በሁዋላ፣ የካታሎጉ ቅጂ በብሌትን መጽሄት እየተባዛ ጥናት ለሚያደርጉ ምሁራን እንዲዳረስ አድርገዋል።
8. የውጭ አገር እርዳታ ለጋሾች እርዳታቸውን በአቆሙ ጊዜ ድርጅቱ የመንግስት ባጀትን ለማግኘት ይችል ዘንድ ለመንግስት አመልክተው በባህል ሚኒስቴር መስሪያቤት ስር ፲፱፻፸ ዓ. ም. ጀምሮ እንዲመደብ አድርገዋል።

ይህን ሁሉ አገልግሎት ካበረከቱ በኋላ ዶ/ር ሥርግው ከመንግሥት የሚገኘው ባጀት ምንም ያህል የድርጅቱን ስራ ሊያንቀሳቅሰው አለመቻሉን በመረዳታቸው፣ ለምርምርና ጥናት ስራ ወደ አውሮፓ ሄደው ጠቃሚ የጥናት ስራዎችን በማከናወን "Book Making in Ethiopia" የተባለ አዲስ መጽሀፍ በ፲፱፻፸፪ ዓ. ም. አሳተሙ። መጽሀፉ በኢትዮጵያ የጥንት ዘመን መጻህፍት እንዴት እንድሚዘጋጁ፣ ብራናው፡ ቀለሙና ብእሩ እንዴት እንደሚሰናዳ በብቃት የሚያስረዳ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ከአውሮፓም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው መደበኛ የመንግስት ስራ ከመጀመራቸው በፊት ለጥቂት አመታት ያህል በግል የምርምር ተግባራቸውን ሲያከነውኑ ቆይተዋል።

በኋላም በ፲፱፻፸፱ ዓ. ም. በወቅቱ የድርጅቱ ስራአስኪያጅ በነበሩት ግለሰብ (በአቶ ፍቅረድንግል በየነ) አስተባባሪነትና ክትትል የኮንትራት ስራ ባጀት እንዲፈቀድ ተደርጎ፣ ዶ/ር ሥርግው ቀደም አድርገው ወጥነውት የነበረውን የቤተክርስቲያን መዝገበቃላት እንዲያጠናቅቁት የቀረበላቸውን ጥሪ በበጎ ፈቃደኝነት ስለ ተቀበሉት፣ በተለመደው የስራ ወዳድነት መንፈሳቸውና ከፍተኛ የእውቀት ችሎታቸው የመዝግበቃላቱን ስራ በመሪነት ጀመሩ። ዶ/ር ሥርግው ለአገራቸውና ለቤተክርስቲያናቸው ባላቸው ፍቅር ይህን በአስራ አራት ጥራዝ የተዘጋጀውን ስራቸውን በ፲፱፻፹፪ ዓ. ም. አጠናቀው አበረከቱ።

ይህ በ እንዲህ እያለ፣ ወደ አሜሪካና አውሮፓ ሄደው የጥናትና የህትመት ስራቸውን ቢያከናውኑ የተሻለ ውጤት ላይ ለመድረስ እንደሚረዳቸው በምመን በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ወደዚያው ሄዱ። ከዚያም ወዲህ ወደ አገረቸው ሳይመለሱ በ፲፱፻፺፭ ዓ. ም. በጀርመን አገር ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው በዚያው በጀርመን አገር መቀበረቸውን በአሳዛኝ ዜና ተረዳን። ዶ/ር ሥርግውን የመሰለ ታላቅ ሰው (Great Man) ሲ.ታጣ ጉዳቱ የዘመድና የወዳጅ ብቻ ሳይሆን፣ በጠቅላላው የአገርና የወገንም ነው። በመሆኑም ሁላችንም እንጽናና ዘንድ እግዚአብሔር ተተኪ መምህር ይዘዝልን።

አቶ ፍቅረድንግል በየነ
አዲስ አበባ